በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፬

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ታህሳስ ፱ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፬

- የጌታችን የትውልድ ሐረግ በተጻፈበት በማቴ 1 ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ድረስ የወደንዶችና የሦስት ሴቶች ሐረግ ተጽፎልናል፡፡ ሦስቱ ሴቶችም ሩት፣ ረዓብና፣ ትዕማር ናቸው፡፡
- ወንዶች በሚጠቀሱበት የትውልድ ሐረግ እነዚህ ሦስቱ ሴቶች ልዩ ሥፍራ ተሰጥቶአቸዋል፤ እኛም ይህንኑ መሠረት በማድረግ መጽሐፈ ሩትን እንማራለን፡፡
- መጽሐፈ ሩት ከመጽሐፈ መሳፍትን ቀጥሎ የሚገኝ መጽሐፍ ሲሆን ጌታችን ከአሕዛብ ወገን ከሆኑት ከሩትና ከራኬብ (ረዓብ) ወገን መወለዱ ዓለምን ሁሉ ለማዳን የመጣ ሕዝብና አሕዛብን የታረቀና ያስታረቀ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡
- መጽሐፈ ሩት አራት ምዕራፍ ብቻ ያለው ቢሆንም እጅግ የሚወደድ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉም በዘመነ መሳፍንት የተጻፈ ሲሆን በየትኛውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የማናገኛቸው የፍቅር መልእክቶች የሚገኙበት መጽሐፍ ነው፡፡
- በመጽሐፉ በመስማማትና በመግባባት የማይታወቁ አማትና ምራት በኑኃሚንና በሩት በኩል ተስማምተው ተፋቅረው እናነባለን፡፡ ሩት እስራኤላዊውን ቦዔዝን አግብታ በንጉሥ ዳዊት በኩል የጌታችን የሴት አያት ሆና ለመቆጠር በቅታለች፡፡
- በዚህ መጽሐፍ ኑኃሚን የእናት ቤተ ክርስቲያናችን ምሳሌ ስትሆን እርስዋም ቦዔዝ ኢየሱስ ክርስቶስን ሩትን ለሚመስሉ የክርስቲያኖች ነፍሳት ሁሉ ያስተዋወቀች ናት፡፡ ሩት የክርስቲያን ነፍሳትን የምትወክል ስትሆን በጋብቻ በኩል ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አዋሕዳናለች፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፪

- በሌላ በኩል ኑኃሚን የብሉይ ቤተ መቅደስ ምሳሌ ስትሆን ሩት ደግሞ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት፡፡ ሁለቱም በቦዓዝ ክርስቶስ በኩል ተዋሕደዋል፤ የብሉይ ቤተ መቅደስና የአዲስ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አንድ ሆነዋል፡፡ ከመጽሐፉም ፍቅርን፣ እምነትንና ቃለ እግዚአብሔርን እናገኛለን፡፡
- ‹‹እንዲህም ሆነ መሳፍንት ይፈርዱ በነበረ ጊዜ በአገሩ ላይ ራብ ሆነ። አንድ ሰውም ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋር በሞዓብ ምድር ሊቀመጥ ከቤተ ልሔም ይሁዳ ተነሥቶ ሄደ። የሰውዮውም ስም አቤሜሌክ፥ የሚስቱም ስም ኑኃሚን፥ የሁለቱም ልጆች ስም መሐሎንና ኬሌዎን ነበረ የቤተ ልሔም ይሁዳም የኤፍራታ ሰዎች ነበሩ። ወደ ሞዓብም ምድር መጡ በዚያም ተቀመጡ።›› ***ሩት 1፡1-2፡፡***
- ይህ ቤተ ሰብ ከእስራኤል ወገን የሆነ በቤተልሔም የኖረ ቤተሰብ ሲሆን ይህች ከተማም የንጉሡ የዳዊትና ጌታችንም የተወለደባት ከተማ ናት፡፡
- እነዚህም በረሐብ የተነሳ ወደ ሞዓብ ምድር መጡ፡፡ ሞዓብ በእስራኤል ዙሪያ በሚኖሩ በፍልስጥኤማውያን መንደር የምትገኝ የአሕዛብ ሥፍራ ናት፡፡
- በካርታ ላይ ስንመለከት ቤተልሔም በሙት ባሕር በምዕራብ ሞዓብ ደግሞ በምሥራቅ ሆና ወደ ሞዓብ ለመሄድ ባሕር መሻገር ያስፈልግ ነበር፡፡
- አቤሜሌክም የበረከትዋን ቦታ ለቆ በረሐብ የተነሳ ወደ ሞዓብ ተሰደደ፡፡ ይህም የጸጋው ግምጃ ቤት የሆነች ቤተ ክርስቲያንን ትተው የሥጋ ፈቃዳቸውን ለመሙላት ወደ ዓለም የሚሄዱትን ያስታውሰናል፡፡ አቤሜሌክና ሁለቱ ልጆቹ መሐሎንና ኬሌዎን ሞቱ፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፪

- **ኑኃሚንም ከአሕዛብ ወገን ካገቡአቸው ከሞዓብ ከሆኑት ከልጆቿዋ ሚስቶች (ምራቶች) ጋር ብቻዋን ቀረች፡፡ አሥር ዓመትም አብረው ተቀመጡ፡፡ በመጨረሻም ኢየሩሳሌምን ትተው መውጣታቸው ስህተት እንደነበር ኑኃሚን ተረዳች፡፡**
- ‹‹እርስዋም በሞዓብ ምድር ሳለች እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ጐበኘ እንጀራም እንደ ሰጣቸው ስለ ሰማች፥ ከሞዓብ ምድር ልትመለስ ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ተነሣች። እርስዋም ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ከተቀመጠችበት ስፍራ ወጣች ወደ ይሁዳም ምድር ሊመለሱ በመንገድ ሄዱ። ኑኃሚንም ምራቶችዋን፦ ሂዱ፥ ወደ እናቶቻችሁም ቤት ተመለሱ በእኔና በሞቱት እንዳደረጋችሁ፥ እግዚአብሔር ቸርነት ያድርግላችሁ።›› ***ሩት 1፡6-8፡፡***
- **ኑኃሚን ባልዋ የሠራውን ስህተት ለማረም ስትነሳሳ ከማስተማር ጋር ለሌሎች ፍላጎት መሟላት ያደረገችውን እንማራለን፡፡**
- ‹‹እግዚአብሔር በየባላችሁ ቤት ዕረፍት ይስጣችሁ አለቻቸው። ሳመቻቸውም ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው አለቀሱ። እነርሱም፦ ከአንቺ ጋር ወደ ሕዝብሽ እንመለሳለን አሉአት። ኑኃሚንም አለች። ልጆቼ ሆይ፥ ተመለሱ ለምን ከእኔ ጋር ትሄዳላችሁ? ባሎቻችሁ የሚሆኑ ልጆች በሆዴ አሉኝን? ልጆቼ ሆይ፥ ተመለሱ ባል ለማግባት አርጅቻለሁና ሂዱ ተስፋ አለኝ ብል፥ ዛሬ ሌሊትስ እንኳ ባል ባገባ፥ ወንዶች ልጆችም ብወልድ፥ እነርሱ እስኪያድጉ ድረስ ትቆያላችሁን? ስለ እነርሱስ ባል ማግባት ትተዋላችሁን? ልጆቼ ሆይ፥ እንዲህ አይደለም የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ወጥቶአልና ከእናንተ የተነሣ እጅግ ተመርሬአለሁ።›› ***ሩት 1፡9-13፡፡***
- **በዚህም ክፍል እርስዋና ባልዋ አቤሜሌክ በሠሩት ስህተት የተነሳ እግዚአብሔር እየቀጣቸው መሆኑን በአማንሳት አስረዳቻቸው፡፡ እንደ ዔሊና አቤሜሌክ ያሉ ሰዎች ለልጆቻቸው የሚጠነቀቁ አልነበሩም፡፡ ዔሊ ለአፍኒንና ፊንሐስ ብሎም ለራሱ፣ አቤሜሌክም ለመሐሎንና ኬሎዎን ብሎም ለራሱ መጥፋት ምክንያቶች ነበሩ፡፡**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፪

- ‹‹ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው እንደ ገና አለቀሱ ዖርፋም አማትዋን ሳመች ሩት ግን ተጠጋቻት። ኑኃሚንም። እነሆ፥ ባልንጀራሽ ወደ ሕዝብዋና ወደ አማልክትዋ ተመልሳለች አንቺም ደግሞ ከባልንጀራሽ ጋር ተመለሽ አለቻት።›› ***ሩት 1:14-15::***
- **ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሁለት ሰዎች አብረው ቢጸልዩም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንደ ዖርፋ ሳይፈጽሙ ሲቀሩ እንመለከታቸዋለን፡፡ ዖርፋ መጀመሪያ ላለመለየት የፈቀደች ብትሆንም በሁለተኛው ጥያቄ ግን ለምን ጊዜዬን አጠፋለሁ፣ ወደማላውቀውስ አገር ስለምን እሄዳለሁ በሚል ሐሳብ ተመርታ ለመለየት ወሰነች፡፡**
- **ሩት ግን ፍቅር ስሜትና ንግግር ሳይሆን ተግባር እንደሆነ ታውቃለችና ኑኃሚንን** ‹‹ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና፥ በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺም ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል›› ***ሩት 1:16*** **አለቻት፡፡**
- **ሩትም አቅዳ የወሰነችው ውሳኔዋን ገለጸች እንጂ ዝም ብላ ንግግርን ብቻ አላስተላለፈችም፡፡ ሩት ወደ ቤተሰቦችዋ፣ አገርዋ ወይም ወደ ባዕዳን አማልክትዋ መመለስ ቢቀላትም ከኑኃሚን ጋር እሄዳለሁ በማለት ከባዱን ውሳኔ ወሰነች፡፡ ባል፣ ቤት፣ ቋንቋ... የሉም፡፡ ሩት አብርሃም ያደረገውን አደረገች፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ውጣ አለው እንጂ ወዴት እንደሚደርስ ቀድሞ አልነገረውም፤ እርሱም ተከተለው፡፡ ሩትም ይህን አደረገች፡፡ ይህም ከፍቅር የመነጨ እምነት ምልክት ነው፡፡**
- **ዛሬ እኛ እንደምናስበው ብናስብ ትመለስ ነበር፤ ምክንያቱም ከውሳኔዋ የምታተርፈው ቁሳዊ ነገር የለምና፡፡ አብርሃምና ሩት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፣ የጠየቀንን ሁሉ እናደርጋለን አሉ፡፡**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፪

- ‹‹በምትሞችበትም ስፍራ እሞታለሁ፥ በዚያም እቀበራለሁ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ እንዲሁም ይጨምርብኝ አለች።›› ***ሩት 1:17፡፡***
- **በኑኃሚንና በሩት መካከል የሚታየው ይህ ፍቅር ከየት ተገኘ? በሀገራችን ባሕል አማችና ምራት እንዲህ አይፋቀሩም፡፡ የሁለቱ ፍቅር መሠረቱም መንፈሳዊ ፍቅር ነበር፡፡**
- ‹‹ኑኃሚንም ከእርስዋ ጋር ለመሄድ እንደ ቈረጠች ባየች ጊዜ እርስዋን ከመናገር ዝም አለች። ሁለቱም እስከ ቤተ ልሔም ድረስ ሄዱ። ወደ ቤተ ልሔምም በደረሱ ጊዜ የከተማይቱ ሰዎች ሁሉ ስለ እነርሱ። ይህች ኑኃሚን ናትን? እያሉ ተንጫጩ። እርስዋም፡- ሁሉን የሚችል አምላክ አስመርሮኛልና ማራ በሉኝ እንጂ ኑኃሚን አትበሉኝ። በሙላት ወጣሁ፥ እግዚአብሔርም ወደ ቤቴ ባዶዬን መለሰኝ እግዚአብሔር አዋርዶኛልና፥ ሁሉንም የሚችል አምላክ አስጨንቆኛልና ኑኃሚን ለምን ትሉኛላችሁ? አለቻቸው። ኑኃሚንም ከእርስዋም ጋር ከሞዓብ ምድር የተመለሰችው ሞዓባዊቱ ምራትዋ ሩት ተመለሱ። የገብስም መከር በተጀመረ ጊዜ ወደ ቤተልሔም መጡ።›› ***ሩት 1:18-22፡፡***
- **በርግጥ ከቤተልሔም የወጡት ከመንፈሳዊነት ተራቁተው ሲሆን ስትመለስ ግን ሩትን ይዛ ሙሉ ሆና የተመለሰች ቢሆንም ኑኃሚን የተረዳችው ተቃራኒውን ነበርና ባዶዬን መለሰኝ አለች፡፡**
- **ይህን የእግዚአብሔር ቁጣና ቅጣት አድርጋ በመቁጠር ቢቀጣትም እግዚአብሔርን በማክብር ተናገረች፡፡**
- **እስራኤል ፋሲካን ቀዳሚት ቀን ካከበሩ በኋላ በሚቀጥለው ቀን - እሁድ የገብስ መከር በዓል ያደርጉ ነበር፤ ይህም ከበዓለ ጰንጠቆስጤ አምሳ ቀን በፊት ነው፡፡ ይህም ኑኃሚንና ሩት ከሞዓብ ወደ ቤተ ልሔም የተመለሱበትን ወርኃ መጋቢትን ያስታውሰናል፡፡ ይህም ቀን የጌታችን ትንሣኤ ነው፡፡**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፬

- ‹‹ለኑኃሚንም ባል የሚዘመደው ከአቤሜሌክ ወገን የሆነ ኃያል ሰው ስሙ ቦዔዝ የተባለ ሰው ነበረ። ሞዓባዊቱም ሩት ኑኃሚንን፦ በፊቱ ሞገስ የማገኘውን ተከትዬ እህል እንድቃርም ወደ እርሻ ልሂድ አለቻት። እርስዋም፦ ልጄ ሆይ፥ ሂጂ አለቻት። ሄደችም፥ ከአጫጆችም በኋላ በእርሻ ውስጥ ቃረመች እንደ አጋጣሚውም የአቤሜሌክ ወገን ወደ ነበረው ወደ ቦዔዝ እርሻ ደረሰች።›› ***ሩት 2:1-3::***
- **ሩት ማንንም አላውቅም፣ ቋንቋቸውን አላውቅም ወዘተ የምትል አልነበረችም፤ እግዚአብሔር ያደረገውም በድንገት የሆነ አልነበረም። ሩት ቦዔዝ ማን እንደሆነ ባታውቅም ለመቃረም ወደ ቦዔዝ እርሻ ደረሰች።**
- ‹‹እነሆም፥ ቦዔዝ ከቤተ ልሔም መጣ፥ አጫጆችንም። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን አላቸው። እነርሱም፦ እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው መለሱለት።›› ***ሩት 2:4::***
- **ቦዔዝ ሠራተኞቹን እግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን ሲላቸው እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው መለሱለት፤ ይህም እግዚአብሔር የሚከብርበት የሰላምታ ዓይነት ነው።**
- ‹‹ቦዔዝም በአጫጆች ላይ አዛዥ የነበረውን ሎሌውን፦ ይህች ቆንጆ የማን ናት? አለው። የአጫጆቹም አዛዥ። ይህችማ ከሞዓብ ምድር ከኑኃሚን ጋር የመጣች ሞዓባዊቱ ቆንጆ ናት እርስዋም፦ ከአጫጆቹ በኋላ በነዶው መካከል እንድቃርምና እንድለቅም፥ እባክህ፥ ፍቀድልኝ አለች መጣችም፥ ከማለዳም ጀምራ እስከ አሁን ድረስ ቆይታለች በቤትም ጥቂት ጊዜ እንኳ አላረፈችም አለው።›› ***ሩት 2:5-7::***
- **ሩት ገንዘብ አልጠየቀችም፤** ‹‹ቦዔዝም ሩትን፦ ልጄ ሆይ፥ ትሰሚያለሽን? ቃርሚያ ለመቃረም ወደ ሌላ እርሻ አትሂጂ፥ ከዚህም አትላወሺ፥ ነገር ግን ገረዶቼን ተጠጊ።›› ***ሩት 2:8::*** **ይህን ለክርስቲያን ነፍሳት እኔ የነፍሳችሁ፣ የእርካታችሁም ሁሉ ምንጭ ነኝ ብሎ የሚናገረን ቦዔዝ - የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው።**

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፬

- ሩት ከቃርሚያው በምትሰበስበው ራስዋንና አማትዋን ለመመገብና ለመርዳት ብቻ የምትፈልግ ነበረች፡፡ ቦዔዝም ወደ ገረዶቼ ተጠጊ አትራቂ በማለት ሰይጣን ከቤ/ክ ሰዎች፣ ከቤተ ክርስቲያን ነጥሎ ብቻችንን አስቀርቶ እንዳይመታን ከክርስቶስ ጋር በኅብረት እንድንኖር ከቤ/ክ እንዳንርቅ አስተምሮናል፡፡
- ‹‹ወደሚያጭዱበትም ስፍራ ተመልከቺ፥ ተከተያቸውም እንዳያስቸግሩሽም ጕበዛዝቱን አዝዣለሁ በተጠማሽም ጊዜ ወደ ማድጋው ሄደሽ ጕበዛዝቱ ከቀዱት ውኃ ጠጪ አላት።›› ***ሩት 2፡9፡፡*** እግዚአብሔር ይጠብቅሻልና ማንም እንዳይነካሽ አዝዣለሁ አለ፡፡ ሲጠማሽም ወደ ማድጋው ሄደሽ ጎበዛዝቱ ከቀዱት ውሃ ጠጪ አላት፡፡ በሁለቱም በኩል ቦዔዝ ስላሚያደርግላት ጥበቃው ገለጠላት፤ ይህም ክርስቶስ ጥበቃውን ፈልጋ ለምትቀርብ ነፍስ የሚያደርግላትን ጥበቃ ያመለክተናል፤ ማንም እንዳይነካት እንዳይጠማትም ይጠብቃልና፡፡
- ‹‹በግምባርዋም ተደፍታ በምድር ላይ ሰገደችለት። እኔንስ ለመቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስ አገኘሁ? እኔ እንግዳ አይደለሁምን? አለችው።›› ***ሩት 2፡10፡፡*** በዚህም ስለ ትሕትናና ስለ እግዚአብሔርን ጸጋ እንማራለን፡፡
- ምንም ሳይገባት እግዚአብሔር ለጸጋው - ለስጦታው የምትበቃ እንድትሆን አድርጓታልና፡፡
- ‹‹ቦዔዝም። ባልሽ ከሞተ በኋላ አባትሽንና እናትሽን የተወለድሽባትንም ምድር ትተሽ ቀድሞ ወደማታውቂው ሕዝብ እንደ መጣሽ፥ ለአማትሽ ያደረግሽውን ነገር ሁሉ ፈጽሞ ሰምቻለሁ። እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኚ በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን አላት።›› ***ሩት 2፡11፡12፡፡***
- በእግዚአብሔር ፊት የሠራነው ሥራችን ሁሉ አይረሳብንም፡፡ ሩት በቅድሚ ጸጋ እግዚአብሔርን ሽታ ካገኘች በኋላ ሌላው ተጨምሮ ተሰጣት፡፡

# መጽሐፈ ሩት - ክፍል ፪

- ‹‹እርስዋም፡- ጌታዬ ሆይ፥ ከባሪያዎችህ እንደ አንዲቱ ሳልሆን አጽናንተኸኛልና፥ የባሪያህንም ልብ ደስ አሰኝተሃልና በዓይንህ ሞገስ ላግኝ አለችው። በምሳም ጊዜ ቦዔዝ። ወደዚህ ቅረቢ ምሳ ብዪ፥ እንጀራሽንም በሆምጣጤው አጥቅሽ አላት። በአጫጆቹም አጠገብ ተቀመጠች የተጠበሰም እሸት ሰጣት፥ በልታም ጠገበች፥ አተረፈችም። ደግሞም ልትቃርም በተነሣች ጊዜ ቦዔዝ ጐበዛዝቱን። በነዶው መካከል ትቃርም፥ እናንተም አታሳፍሩአትደግሞ ከነዶው አስቀርታችሁ ተዉላት እርስዋም ትቃርም፥ አትውቀሱአትም ብሎ አዘዛቸው። በእርሻውም ውስጥ እስከ ማታ ድረስ ቃረመች የቃረመችውንም ወቃችው አንድ የኢፍ መስፈሪያ ያህልም ገብስ ሆነ። ተሸክማውም ወደ ከተማ ገባች፥ አማትዋም የቃረመችውን አየች ከጠገበችም በኋላ የተረፋትን አውጥታ ሰጠቻት። አማትዋም። ዛሬ ወዴት ቃረምሽ? ወዴትስ ሠራሽ? የተቀበለሽ የተባረከ ይሁን አለቻት። እርስዋም፡- ዛሬ የሠራሁበት ሰው ስም ቦዔዝ ይባላል ብላ በማን ዘንድ እንደ ሠራች ለአማትዋ ነገረቻት። ኑኃሚንም ምራትዋን፡- ቸርነቱን በሕያዋንና በሙታን ላይ አልተወምና በእግዚአብሔር የተባረከ ይሁን አለቻት። ኑኃሚንም ደግሞ። ይህ ሰው የቅርብ ዘመዳችን ነው፥ እርሱም ሊቤዡን ከሚችሉት አንዱ ነው አለቻት። ሞዓባዊቱ ሩትም። ደግሞ። መከሬን እስኪጨርሱ ድረስ ጐበዛዝቴን ተጠጊ አለኝ አለቻት። ኑኃሚንም ምራትዋን ሩትን፡- ልጄ ሆይ፥ ከገረዶቹ ጋር ብትወጪ፥ በሌላም እርሻ ባያገኙሽ መልካም ነው አለቻት። ሩትም የገብሱና የስንዴው መከር እስኪጨረስ ድረስ ልትቃርም የቦዔዝን ገረዶች ተጠጋች በአማትዋም ዘንድ ትቀመጥ ነበር።›› ***ሩት 2:13-14፡፡***

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org